# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ - መኢሶን -

# ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME´SONE)

## ቃለ መጠይቅ ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር

### ያለፈውና መጪው ትግል

፩ኛ. የወቅቱ የፖለቲካ ሂደት

፪ኛ. ቀይ ሽብር

፫ኛ. መኢሶን፤ ሶቭየቶችና ኢትዮጵያ በ 1969

፬ኛ. መኢሶን ተሸንፏል ? ከኢሕአፓ በምን ይለያል ?

ለአንባቢዎች፡- ይህ ቃለ መጠይቅ ቀደም ሲል በጦቢያ መጽሄት በቅጽ 2 ከቁጥር 11 እስከ 12 1986፤ በቅጽ 3 ከቁጥር 1 እስከ 3 1986 በተከታታይ የወጣ ሲሆን፤ ብዙ በውጭ የሚገኙ አምስቱንም ቁጥሮች ተሟልተው ያላገኙ አንባቢዎች ድርጅታችንን በየጊዜው ከመጠየቃቸውም በላይ፤ በበኩላችንም ይህ የቃለ መጠይቅ ጽሑፍ ለአንዳንድ ጉዳዮች የውይይት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ያስጨብጣል ብለን ስለገመትን፤ ጽሁፉን አሰባስበን በዚህ መልክ አቅርበነዋል።

መልካም ንባብ

1987

# ያለፈውና መጪው ትግል

ዶክተር ነገደ ጎበዜ ደባባስ፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት በተለይም በግራ ኃይሎች እንቅስቃሴና በ17ዓመቱ የስደት ዘመን ስማቸው ከማይጠቀሱ ሰዎች አንዱ ናቸው፡፡ ከመኢሶን አመራር አባሎች አንዱ ሲሆኑ፣ የፓሪሱ እርቅና ሰላም ጉባኤ ሊቀመንበር ናቸው፡፡ ባለፈው ሰሞን የወቅቱን የአገራችንን የፖለቲካ ሂደትና ያለፈውንም ትግል በተመለከተ ለተደረገላቸው ቃለመጠይቅ ምላሽ ሰጥተው ነበር፡፡ ለወቅቱ የፖለቲካ ሂደት አንመፍትሔው ለማየት፣ ያለፈውን ለመቃኘት ጠቃሚ ነው፡፡ ወደውይይቱ እንግባ፡፡



## የወቅቱ የፖለቲካ ሂደት

ጥያቄ፦ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የጀመሩት መቼ ነው?

መልስ፦ እንደተወለድ ቀን ነዚህ እለት በዚህ ሰዓት የፖለቲካ ትግል ጀመርኩ ማለት አይቻልም፡፡ በጃንሆይ መንግሥት ሥር የነበረው ግፍ በተለይ ደግሞ የመሬቱ ስሪት ጉዳይ አስቀይሞኝ በሆዱ የሸፈትሁበትን ጊዜ ዛሬ አላስታውስም፡፡ በጣም ረዥም ጊዜ ሳይሆነው አይቀርም፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ግን በፖለቲካ ጉዳይ ሰልፍ የወጣሁት አይረሳኝም፡፡ በእንጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነበር፣ የዛሬ ሰላሳ ሦስት ዓመት፡፡ ያን ጊዜ ገና የ17 ዓመት ወጣት ሆኜ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ይባል የነበረው የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ነበርኩ፡፡ ከዚያች ቀን ጀምሮ ሌት ተቀን ታግያለሁ ወይም በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ስትራመስ ኖሬያለሁ ማለት አይደለም፡፡ ከዚህ ጊዜ አንስቶ ፊውዳሊዝምን ለመዋጋት ከተነሳው የያኔው ትውልድ ጋር ቀስ በቀስ አብሬ ወደፖለቲካው ዓለም ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ የሆኖ ሆኖ በጣም ረዥም ጊዜ ነው፡፡ አንዳንዴ ለራሴም ይገርመኛል፡፡ ያኔ በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ዛሬ ካሉት ዜጎች ከመንግሥት በኩል ይሁን ከተቃዋሚው አብዛኞቹ ገና ልጆች ነበሩ፡፡ ጥሩ ቁምነገርም የታጠቁ አይመስለኝም፡፡

ጥያቄ፦ በዚህን ጊዜ ሁሉ አንድ አቋም ይዘው ታግለዋል ወይስ. . .?

መልስ፦ በእውነቱ ከዳር እስከዳር አንድ አቋም ማለት ያስቸግራል፡፡ አንድ ዓላማ ግን አለን፡፡ «ኢትዮጵያ» የማለው ሃሳብና ከዚያ ተያይዞ የሚመጣው የሀገር ፍቅር፣ ከዚህም የሚወለደው ይቺ አገር የበለጸገች ሀገር እንድትሆን፣ኩሩ አገር እንድትሆን፣ የተከበረች አገር እንድትሆን ሌት ተቀን መመኘት፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ ስኖር እንግዲህ ወደ ሰላሳ ዓመት ሊሆነኝ ነው፡፡ ግን እንደኔ ውጭ ብዙ የቆዩ ዜጎች የማያውቁት ስሜት አለ፡፡ የሀገር ፍቅር ስሜት እንደግለሰብ ፍቅር፣ ፈረንሳዮች እንደሚሉት «ከዓይን የራቀ ከልብ ይርቃል» አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም ተቃራኒው ይመስለኛል፡፡

ሀገር ፍቅር ግን ብቻውን ወደፖለቲካ ትግል አያስገባም፡፡ አገሬ ትበልጽግ፣ አገሬ ኩሩ ትሁን፣ የተከበረች ትሁን የሚል ዜጋ ሁሉ ከብሩስ፣ ብልጽግናውስ እንዴት ነው? ብሎ ራሱን እስካልጠየቀ ድረስ ከሰው ሳይደርስ በሰላም በሆዱ አገሩን እየወደደ ሊኖር ይችላል፡፡ ትግልና ችግር የሚመጣው ለዚህ አገር ፍቅር ተጨባጭ ይዘትና ትርጉም ለመስጠትና ለዚህም እውንነት መታገል ሲጀመር ነው፡፡ ያን ጊዜ በሀገር ፍቅራቸው የማይተናነሱ ዜጎች ወይም ቡድኖች ለዚህ ዓላማቸው የተለያየ ይዘት ለሰጡና ሊሰጡ፣ ሊታገሉ ይችላሉ፡፡

እኔ ለሀገር ፍቅር የምሰጠው ትርጉምና ይዘት የህዝብ ፍቅር ነው፡፡ የሕዝብ ፍቅሬ ደግሞ ወገናዊ ነው፡፡ ለሕዝብ እድገት፣ ለሕዝብ ብልጽግና፣ ለማኅበራዊ ፍትህና ለእኩልነት መታገል ነው ለኔ ሀገር ፍቅር ማለት፡፡ በዚህ በኩል ምንም ለውጥ አላደረግሁም፡፡ ይህ እንዴት ከሥራ ላይ ይውላል በሚለው ጥያቄ ግን ብዙ ለውጦች አድርጌያለሁ፡፡ የአቋም ለውጥ ሊባል ይቻላል፡፡

እኔ ብቻ ሳልሆን አንድ ትውልድ እንዳለ ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሔ የሶሻሊስት አብዮት ብቻ ነው ብሎ ከልቡ አምኖበት ታግሏል፣ ተሰውቷል፡፡ ለተራበው፣ ለተጨቆነው ፍትህ ለተነሳው ሕዝብ ማለትም ለገበሬው፣ ለወዛደሩ ወገናዊነቱን እየገለጸ ለዚህ አብዮት መሳካት ያለ የሌለ ኃይሉ፣ ሕይወቱን ጭምር የከሰከሰ ትውልድ ነው፡፡ በወዝ አደሩ የበላይነት በአርሶ አደሩ ተባባሪነት. . . እያልን ታግለናል፡፡ ዛሬ ደግሞ የሕግ የበላይነት፣ የብዙ ፓርቲዎች ዲሞክራሲ፣ እንላለን፡፡ በኔ በኩል ይህ የአቋም ለውጥ «የሶሻሊስቱ አብዮት ካልተሳካ እስኪ ጽድቁ ይቅርና በወጉ ይኩንነን፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንሞክር» ከሚል አስተሳሰብ የፈለቀ ለውጥ አይደለም፡፡ ወይም ደግሞ እስኪ ለጊዜው፣ ለታክቲክ ዲሞክራሲ እንበልና በዚህ ተጠቅመን ሶሻሊስት ሥርዓት እንገንባ ከሚል ስትራቴጂ ተነስቼም አይደለም፡፡

ዓለም ውስብስብ ነች። ለአንድ ህብረተሰብ ነጻነት ብለው የሚነሱ ኃይሎች በዚህ በእኩልነት ስም ነጻነትን ሲያወድሙ፣ የኤኮኖሚ እድገት እየተባለ ማኅበራዊ ፍትህ ደብዛው ሲጠፋ፣ በዚህ ተመርተው ሕዝብ መርተው ሥልጣን የሚይዙ ኃይሎች ደግሞ ማኅበራዊ ፍትህ እናመጣለን ብለው፣ እኩልነት እናሰፍናለን ብለው ተነስተው በተግባር ግን እድገት ሲገታና ሁሉም በእኩልነት ሲቆረቁዝ አይተናል። ነጻነት፣ እኩልነት፣ እድገት፣ ማኅበራዊ ፍትህ ሁሉም የሚፈለጉ ጸጋዎች ናቸው። ግን ችግሩ ብዙ ጊዜ ሲቃረኑ እናያቸዋለን። እንዳመጣጣቸው፣ እንደተጨባጩ የሕብረተሰብ ሁኔታ በተቻለ እነሱን ለማጣጣም መሞከር እንጂ እዚህን ሁሉ በአንድነት የሚያነግስ ሥርዓት አመጣለሁ ማለት አይቻልም። ለዚህ ነው ከወዲሁ አንድ ያለቀለት«ገድፈ ሥርዓት» ይዞ መታገል አስቸጋሪ የሚሆነው። ከዚህ ይልቅ አስቀድሞ ለዲሞክራሲ፣ ምንም ዓይነት «ከፍተኛ ዓላማ» ለማይሸርፈው የሕግ የበላይነት መታገልና በዚህ ክልል ውስጥ እንደ ህዝቡ ምርጫ፣ እንደብዙሃኑ ፍላጐት፣ እንደሀገሪቱ ተጨባጭ የኤኮኖሚ እድገት ሁኔታ ምንጊዜም ወደተሻለ ማኅበራዊ ፍትህ የሚወስድን ፖሊሲ መቀየስና ለሱ መታገል የሚያስፈልገው።

__ጥያቄ__፣ ለምን አዲስ አበባው ጉባዔ ላይ አልተገኙም?

__መልስ__፣ የአስተባባሪው ኮሚቴ ሰብሳቢ እንደመሆኔ መጠን በዚህ ጉባዔ ላይ አለመገኘቴ እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል። እንዳልሄድ ከመወሰኑ በፊት ከትግል ጓደኞቼ ጋር ብዙ ተነጋግረናል። ይህ የጠነሰስነው የሰላም ጉባዔ የማይዋጥ የማይተፋ ነገር የሆነበት ኢህአዴግ ጉባዔውን መከልከል ባይቻለው አንዳንድ መሰናክሎችን በመፍጠር ሊያሰናክል ይችላል የሚል ስጋት ነበረን። በመሆኑም ምንም ዓይነት ሰበብ ላለመስጠት ተስማማን። ከነዚህ ሰበቦች አንዱ እኔን በማይመለከተኝ ቀይ ሽብር ወንጀሉ ለማሰር የነበረው ፍላጐት ነው። «የሰላምና እርቅ ጉባዔው አስተባባሪ ተወንጅለው ታሠሩ» ብሉ ውዥንብር ለመፍጠር። ይህንን እድል ለኢህአዴግ ለመስጠት አልፈለግነም። በነበሩን መረጃዎች እኔን እንደሚያሰሩኝ እርግጠኛ ነበርን። ግን አንድ ነገር ግልጽ መሆን ይኖርበታል። በዚህ ምክንያት አዲስ አበባ አለመግባቴ ወንጀለኛነትን መቀበል አይደለም። የሰዎቹን ዲሞክራትነት በመጠራጠር እንጂ።

ይህ ስለተባለ ቅንጅቱም ሆነ መኢሶን ለዚህ ጉባዔ መጠንሰስና መሳካት፣ በሃገራችን ሰላም እንዲወርድ ያላቸውን ከፍተኛ ጉጉት ለመግለጽ ሲሉ ወደ አዲስ አበባ የላኩት ከፍተኛ ቡድን ነበር። ከኔ የተሻለ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ታጋዮች ናቸው። ይህን ስናደርግ ባወጣ ያውጣቸው ብለን አይደለም። ሰላምና እርቅ ብለው የመጡ ልኡካንን በስመ ቅንጅት አፋፍሶ ያስራል ብለን አልጠበቅንም ነበር። ሰዎቹ ባይገባቸው ነው እንጂ ይህንን ርምጃ ስንወስድ ርዝራዥም ብትሆን ትንሽ ዲሞክራትነት አያጡም፣ ለመድኃኒት ታህልም ብትሆን አንዳንድ የሞራል መርሆዎች ተርፏቸዋል፣ ጠብታም ትሁን የፖለቲካ ብስለት አላቸው ብለን ማመናችን ነበር። ሳየው ከሁሉም አንጻር ተሳስተናል። ምርጥ ታጋዮቻችንን እነገነትን፣ አበራን፣ ገነነውን፣ መስፍንን ለእስር እንድንዳርግ ያደረገን ስህተት ነው። የመኢሶን ዋና ጸሐፊና የቅንጅቱ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ጓድ አበራ የማነአብ ገና በኢህአዴግ እጅ ለብዙ ጊዜ ተንገላቷል። በትግል ዓላማና በሀገር ፍቅር መንፈስ የተገነባውን የቅንጅቱን አንድነት እናላለን ብለው አስበው እንደሆነ ተሳስታችኋል እንላቸዋለን። ጓድ አበራ በሐቀኝነቱና በሕዝብ ፍቅሩ ምንም የማይወጣለት ቆራጥ ታጋይ እንደሆነ እንኳን እኛና እነሱም አሳምረው ያውቁታል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ከለጋ ወጣትነቱ ጀምሮ ባስመዘገበው የትግል ታሪክ የምናፍርበት አንዲትም የፈጸመው ወንጀል የለውም። በምን ተጨባጭ ነገር እንደሚወነጅሉት ጨንቋቸው ነው ነጋ ጠባ ፍርድ ቤት አመላልሰውታል። ከዚህ መሠረታዊ ችግር የሚወጡበት መንገድ በማጣታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው።

__ጥያቄ__፣ ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሔው ምን ይመስልዎታል?

__መልስ__፣ ለኢትዮጵያ ውስብስብ ችግሮች ቀላልና አንድ ወጥ መፍትሔ የለም። ከዚህ በፊት እንዳልኩት ቢኖር እስከዛሬ ይሰማ ነበር። እንኳን መፍትሔው ላይ ችግሩ ምን እንደሆነም መግባባት የለም። በበኩሌ መፍትሔውን ከመትጠይቀኝ ችግራችንን ስለምንፈታበት ዘዴ ብትጠይቀኝ ይሻለኛል። ዘዴው ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ውይይት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ውይይት ደግሞ ለዚህ ወይ ለዚያ ትግር መፍትሔ ለመስጠት አይደለም። ዘላለማችንን ብንወያይ ለሀገራችን ችግሮች ድፍን ኢትዮጵያ የሚስማማበት አንድ መፍትሔ አናገኝም። የውይይቱ ዓላማ አንድ ብቻ ነው። ሁሉም የበኩሉን መፍትሔ ይዞ ለዚያ በሰላምና በዲሞክራሲ የሚታገልበትን መድረክና ክልል በጋራ ስምምነት ለመገንባት ነው። ይህ የጋራ መድረክና ክልል (ፍሬምወርክ) የህጐች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግሥት ነው። ዛሬ የዚህ የህገመንግሥት ጥያቄ የሀገራችን ቁልፍ ጥያቄ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ይመስለኛል። ግን ደግሞ የኔ የግል አስተያየቴ/ ምናልባት እስር ዓመት ያህል ሕግ ስማር ወደመጨረሻው ላይ ያተኰርኩት ሕገመንግሥት ትምህርት ላይ በመሆኑ ይሆናል/ ለዚህ ቁልፍ ጥያቄ ገና በቂ ትኩረት አልተሰጠውም። ይህንን የሰጣችሁኝን አጋጣሚ ተጠቅሜ በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ሃሳቤን ልገለጽ።

የሚረቀቀው ህገ መንግሥት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሚሆንና ለረዥም ዘመን ሊያገለግል ሆኖ መነደፍ እንዳለበት ስምምነት አለ። ይህ ሕግ በአንዲት የታሪክ አጋጣሚ ከሕዝቡ 51 ከመቶ ያገኘ የፖለቲካ ኃይል በተቀረው 49 ከመቶ ላይ የሚጭነው ላይሆን በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካም ሆነ የጥቅም ቡድኖች በሙሉ ተደራድረው በተቻለ መጠን በጋራ ስምምነት የሚያጸድቁት መሆን እንዳለበት የህገ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ያለ አስተሳሰብ ነው። እንደተራ ሕግ በተራ ድምፅ ብልጫ የማይሻር፣ የማይሻሻል ሰነድ ነው። ለዚህም ነው ከወዲሁ ሲረቀቅና ሲጸድቅ በተቻለ በጋራ ስምምነት እንጂ በተራ ድምፅ ብልጫ መሆን የሌለበት።

እንደዚህም በመሆኑ አንድ ህገ መንግሥት ይዘቱ ብቻ ሳይሆን የሚረቀቅበትና የሚጸድቅበት ሂደት በጣም ትልቅ ቦታ ያለው ነገር ነው። እንዲያውም ዛሬ ስለመጭው ህገመንግሥት ይዘት መከራከር ጊዜው አይመስለኝም። ማን የመጀመሪያውን ንድፍ ያርቅቀው የሚለውም ጥያቄ እስከዚህ አንገብጋቢ ጥያቄ አይደለም። ፕሬዚዳንት መለስ ቤት ዘግተው የህገመንግሥት ንድፍ ይኸውላችሁ ቢሉን እኔ ግድ የለኝም። ከሁሉ ቁልፍ ጥያቄ ግን ይህንን ህገመንግሥት ማን ያርቅቀው ሳይሆን ማንና እንዴት ያጽድቀው የሚለው ጥያቄ ነው። ኢህአድግ የራሱን ረቂቅ ማቅረብ ይችላል። አማራጭ አለን የሚሉ ኃይሎች ደግሞ የራሳቸው አማራጭ ረቂቅ አቅርበው በዚያ ላይ በሕዝብ ፊት ክርክሮች ሊካሄዱ ይችላሉ።

ዋናው ጥያቄ ይህ ህገ መንግሥት በህዝብ ነጻና ርትአዊ ምርጫ

በተሰየመ የሕ/መንግሥት ጉባዔ እንዲጸድቅ ማድረጉ ላይ ነው። ዋናው ጥያቄ ብዙሃን ይሁኑ እናሳ፣ ከህብረተሰቡ 40 ከመቶ ይወከሉ፣ 15 ከመቶ የተለያዩ ኃይሎች ሕዝቡ በምርጫው እንደሚሰጣቸው ክብደት እየታየ የሚወከሉበት ጉባዔ ማቋቋሙ ላይ ነው። ከፍ ብዬ የሀገራችን ችግር የሚፈታው በውይይት ነው ስል ይህ ውይይት ሁሉንም አሉ የሚባሉትን ኃይሎች የሚያሳትፍ መሆን እንዳለበት ተቀብዬ ነው። ለዚህ ውይይት አማካይ መድረክ ደግሞ ይኸው የህገ መንግሥት ጉባዔ ሆኖ ይታየኛል።

እንግዲህ ሁለት ነጥቦች አሉ። አንደኛ ነጻና ርትአዊ መርጫ። ሁለተኛ ሁሉንም የሀገሪቱን የፖለቲካና የጥቅም ቡድኖች ያካተተ፣ በነጭና ጥቁር ብቻ ሳይሆን እንደባለቀም ፎቶግራፍ የሀገሪቱን የፖለቲካ፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የባህል ስብስቦች የሚያንጸባርቅ የሕገ መንግሥት አውጭ ጉባዔ መሰየም። ከሁለቱ አንዱ ከጎደለ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነው። ዘላቂ ህገመንግሥት ዘበት ነው።

ችግሩ የኢህአዴግ ሂደት ከምኑም የለበትም። ለነጻ ምርጫ ብሎ ያቀረበው የምርጫ ሕግ ዛሬ መላው ዓለም ከተቀበላቸው የነጻና ርትአዊ ምርጫ መለኪያዎች ጋር ሲገናዘብ ከምኑም የሌለ ሕግ ነው። አማራጭ ኃይሎችም ሆኑ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ አድርገው ነፃና ርትአዊ ምርጫ የሚካሄድበት ሁኔታ ቢፈጠርም ደግሞ ሌላም መጠየቅ ያለብን ነጥብ አለ። የሚመረጠው የሕገ መንግሥት ጉባዔ የረባ የውይይት ጉባዔ እንዲሆንና ሁሉን ያካተተ እንዲሆን ከተፈለገ ኢህአዴግ የመረጠው የምርጫ ሥርዓት /ኤሌክትራል ሲስተም/ ጨርሶ መለወጥ ይኖርበታል።

የመጀመሪያው ነጥብ ላይ ትንሽ ላብራራ። በኢህ/ ዴግ ሂደት ነጻና ርትአዊ ምርጫ አይገኝም። በዚህ ጉዳይ ላይ የኢህአዴግን የምርጫ ሕግ ጉድለቶች ለመጠቆም ብቻ ሳይሆን አንድ ሌላ አማራጭ ሂደት ለመጠቆም እንዲቻል አማራጭ ኃይሎች አንድ ግብረ ኃይል መሰየም ይኖርባቸዋል። የምርጫውን ሕግ ጠልቂ ገና አላጠናሁትም። እንዲሁ ገረፍ ገረፍ ሳደረገውና በተለይ ደግሞ እንዲሁ እንደኛው ከረዥም ጊዜ ጦርነት ወጥታ ምርጫ ካካሄደችው ከካምቦጅ ሁኔታ ጋር ሳነጻጽረው እጅግ ዓይን የወጡ ጉድለቶች አሉበት።

*መጀመሪያ* ነገር ከወዲሁ መጠየቅ ያለበት የኢህአዴግ ህግ እንደሚለው ታዛቢዎች እነዲኖሩ ሳይሆን ሂደቱንም ሆነ ምርጫውን የሚቆጣጠሩ የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ ተወካዮች ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ ነው። በካምቦድያ የተደረገው እንደዚህ ነው።

*ሁለተኛ* ለመወዳደር የሚሹ ፓርቲዎች ሁሉ በነጻነት መወዳደር መቻል አለባቸው። የኢህአዴግ ሕግ ይህንን አያረጋግጥም። በተለይ የፓርቲዎች ሕግ የተባለው የሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች /ጸረ ሰላም የሆኑ፣ ኢትዮጵያ የተፈራ ረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ውሉች የሚቃወሙ. . . /እያለ ብዙ ይደረድራል። ችግሩ መስፈርት ማስቀመጡ ላይ አይደለም። አንድ ድርጅት የተባሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለማሟላቱን የሚወስነው ራሱ ኢህአዴግ መሆኑ ነው። በካምቦድያ ይህ ኃላፊነት የተሰጠው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ለተመድ) ነው።

*ሦስተኛ* የማስ ሚዲያው ጥያቄ አለ። ሁሉም ተወዳዳሪዎች በእኩልነት እንዲጠቀሙ ከተፈለገ ወይ አንድ ገለልተኛ ኮሚሽን ወይ ደግሞ ከሁሉም ፓርቲዎች የተውጣጣ አካል መፈጠር ይኖርበታል። በካምቦድያ አሁንም ይህ ኃላፊነት የተሰጠው ለተመድ ነበር። እኛ አገር ግን ለማስታወቂያ ሚኒስትሩ ነው።

*አራተኛ* ገለልተኛ የሆነ የምርጫ ቦርድ ያስፈልጋል። ይህም ከፓርቲዎች የተውጣጣ ሊሆን ይችላል። ወይ እንደ ካመቦድያ በዓለም አቀፍ ኤክስፐርቶች፣ በተመድ ቁጥጥር ሥር የሆነ። እኛ አገር ቦርዱን የሚሰይመው የተወካዮች ምክር ቤት ነው። ሊቀመንበሩን የሚሾመው ፐሬዚዳንቱ ነው።

*አምስተኛ* ሁሉም የተስማማበት የምርጫ ሕግ። ይህ ካልሆነ አንዱ ቡድን ብቻ ባወጣው ደንብ መሠረት ኳስ ግጥሚያ እንደማሄድ ነው። አይሰራም። አሁንም ካምቦድያ ይህ ተግባር በተመድ ተሳትፎ የተካሄደ ነው። እኛ አገር ኢህአዴግ በመሰለው በሚያመቸው ነው የሠራው።

*ስድስተኛ* ነጻና ርትአዊ ምርጫ ስንል ዜጎችን በሙሉ የሚያሳትፍ መሆን አለበት። የኢህአግ ሕግ እስከናካቴው ባለሦስት ማዕረግ ኢትዮጵያውያን ፈጥሯል። አንደኛ ማእረግ ኢትዮጵያው ያን የመምረጥም የመመረጥም መብት ያላቸው። ሁለተኛ ማእረግ ኢትዮጵያው ያን የመምረጥ እንጂ የመመረጥ መብት የሌላቸው። ሦስተኛ ማዕረግ ኢትዮጵያው ያን የመምረጥም የመመረጥም መብት የሌላቸው። ይኸ ሦስተኛው ማእረግ እኛን በውጭ የምንገኘውን ስደተኞች የሚጠቀልል ነው። በኢትዮጵያ ጉዳይ ምንም መብት የለንም ማለት ነው።

*ሰባተኛ* በምዝገባ ጣቢያዎች የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ተወካዮች የሉም። በድምጽ ቆጠራውም ጊዜ እንደዚሁ ሰዝግ ችሎት ነው። ይህ በየትም ምርጫ ያልታየ ጉድ ነው። እንደገና ወደመቦድያ ብንመለስ ተመድ ቀደም ብሎ ባካሄደው የሲቪክ ትምህርት ፕሮግራም ላይ ምዝገባና ቆጠራ ሰዎች ሲያሰለጥን ተወዳዳሪ ፓርቲዎችም በዚህ ተግባር የሚወከሏቸውን በሺህ የሚቆጠሩ አባላት ሰይመው ለእነሱም ስለምዝገባና ስለቆጠራ ልዩ ኮርስ ተሰጥቷል።

*ስምንተኛ* በመርጫው ጊዜ የጸጥታን ጉዳይ በሚመለከት የኢህአዴግ ህግ የሚለው በምርጫው ጊዜ የታጠቁ ሰዎች ከግማሽ ኪሎሜትር በላይ እንዳይጠጉ ብቻ ነው የሚያዘው። በዚያን ሰሞን የታጠቁ ኃይሎች ሁሉ በየጦር ሰፈራቸው ስለመካተታቸው፣ ይህ ደግሞ ከሥራ ላይ እንዲውል ስለሚያስፈልገው ቁጥጥር አያነሳም። አሁንም በካምቦድያ ይህ ተግባር የተሰጠው ለተመድ ነበር።

ከፍ ብየ እንዳልኩት ይህ ሁሉ የኢህአዴግን የምርጫ ህግ እንዲያው ገረፍ ገረፍ ሲያደረጉት የሚታይ ጉድለት ነው። አማራጭ ኃይሎች በርግጥ ለነጻና ርትአዊ ምርጫ የቆሙ ስለሆኑ በዚህ በኩል ያላቸውን አስተሳሰብ በተቀናበረ መልክ ለማቅረብና ሕዝቡን ለመቀስቀስ አንድ የጋራ የሆነ ግብረኃይል አቋቁመው መሥራት ይኖርባቸዋል። ግን ደግሞ የምናወራው ስለመንግሥት መመረጥ ወይም ደግሞ ስለተራ ህግ ሳይሆን ስለህገመንግሥት መጽደቅ እስከሆነ ድረስ በኔ ግምት ነጻና ርትአዊ ምርጫም በቂ አይደለም። ለታህሳሱ ጉባዔ ባቀረብነው ሰነድ ላይ ይኸ በግልጽ ተቀምጧል። መጀመሪያ ለማንኛውም ምርጫ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ መታገል። ከዚያ ተያይዞ ደግሞ ለሕገ መንግሥት ጉባዔ ተስማሚ የሆነ የምርጫ ሥርዓት ያስፈልጋል።ይኸውም በዚያው ሰነድ ላይ እንደተገለጸውና በጉባዔው እንደተጠየቀው የምርጫው ሥርዓት ተመጣጣኝ ውክልና (ፕሮፖርሽናል ሪፕሬዘንቴሽን) መሆን አለበት ማለት ነው። በኔ ግምት ይህ

የሚመሪ ጠው የሕገ-መንግሥት ሸንጐ ሁሉን አቀፍ እንዲሆን፣በኢትዮጵያችን የሚገኙ ኃይሎች ሁሉ የሚወከሉበት እንዲሆን፣ ከዚህም ሸንጐ የሚወጣው ሕገመንግሥት በርግጥ የሀገሪቱ የበላይ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም የጋራሰነድ እንዲሆን ከተፈለገ ይህ የምርጫ ሥርዓት የማይታለፍ ነው። እዚህም ላይ ነገሩ ቢረዝምም ትንሽ ላብራራ እፈልጋለሁ ።

በመሠረቱ ሁለት ዋና ዋና የምርጫ ሥርዓቶች (ኢሌክቶራል ሲስተሞች)አሉ። የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት (ማጆሪቲ ሲስተም)የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት(ፕሮፖርሽናል ሪፕሬዘንቴሽን) እነዚህ ራሳቸው በውስጣቸው ንዑስ ሥርዓቶች አሏቸው። ብዙ ዝርዝር ውስጥ አልገባም።

አንደኛው የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት መሠረት ሀገሪቱ ፓርላማ ውስጥ ባለው ወንበር ልክ በምርጫ ቀበሌዎች ትሸነሸናለች። በፓርላማው ውስጥ አንድ ሺህ ወንበር ካለ በሀገሪቱ አንድ ሺህ የምርጫ ቀበሌዎች ይኖራሉ። አንድ ሺህ ተወካዮች ተመርጠው ወደ ፓርላማ ይመጣሉ። ካየቀበሌ አብዛኛውን ድምፅ ያገኙት ከየምርጫ ያገኙት ግን እንግዲህ የአብዛኛው ድምፅ ሲባል ሁለት ዓይነት ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ አንድ ተመራጭ ከአንድ የምርጫ ክልል ተመርጦ ወደ ፓርላማው እንዲመጣ ከጠቅላላው ድምጽ ከ50 ከመቶ በላይ ማግኘት አለበት። ብዙ ተወዳዳሪዎች ሲኖሩ ማገኛቸውም በመጀመሪያው ዙር ከግማሽ በላይ እያገኙ ይሆናል። ስለዚህ ሁለተኛ ዙር ይዘጋጃል። ከሁሉ ከፍተኛ ድምጽ ያገኙት ሁለት ወይም ሦስት ተወዳዳሪዎች ይቀሩና ሌሎቹ ከውድድሩ ይወጣሉ። ብዙውን ጊዜ ደግሞ በዚህ መልክ ከውድድሩ የሚወጠት «ለኔ ድምጽ የሰጣችሁ ሁሉ ለእገሌ ድምጽ ስጡ» እያሉ ጥሪ ያደርጋሉ። ኢህአዲግ የመረጠው ይህንን እንኳን አይደለም። ፈልፍሉ እንዳመቸው ያወጣው ሥርዓት የዚህ የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት ንዑስ ክፍል የሆነውን «ከፍተኛ ድምፅ» ሥርዓት ልንለው የምንችለውን ነው። አንድ እጩ ከአንድ የምርጫ ቀበሌ «ተመረጠ» ተብሉ ለመምጣት የግድ ከ50 ከመቶ በላይ ማግኘት የለበትም። 20ም 30ም ከመቶ ድምጽ ቢያገኝ ከሌሎቹ ተወዳዳሪዎች ሁሉ ከፍተኛውን ድምጽ ካገኘ ይበቃዋል።, ይህን ንዑስ ስርዓት ኢህአዴግ ለምን እንደመረጠ ዝቅ ብየ ለመጠቆም እሞክራለሁ።

ሁለተኛው የምርጫ ሥርዓት ተመጣጣኝ ውክልና (ፕሮፖርሽናል ሪፕሬዘንቴሽን) ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት መሠረት ለምርጫ የሚቀርቡት በአብዛኛው ግለሰቦች ሳይሆኑ ድርጅቶች ናቸው። በፓርላማው ውስጥ አንድ ሺህ ወንበር ስላለ ሀገሪቱ አንድ ሺህ የምርጫ ቀበሌዎች ተደርጋ አትሸነሸንም። ወይም እንዳለ ሀገሪቱ አንድ የምርጫ ቀበሌ ትሆናለች። ወይም ደግሞ በተወሰኑ ታላላቅ የምርጫ ክልሎች ማለትም አምስት ወይም አስር ወዘተ ቦታ ትሸነሸናለች። ፓርቲዎች በሀገር ደረጃ የቻሉትን ያህል የዜጎች ድምጽ ለማግኘት ይወዳደራሉ። አንድ ፓርቲ በፓርላማው ውስጥ የሚያገኘው ወንበር በጠቅላላ እንዳገኘው ድምጽ ይወሰናል ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ሺህ ወንበር ላለበት ፓርላማ 20 ሚሊዮን መራጭ ካለ አንድ ወንበር ለማግኘት 20ሺህ ድምጽ ማግኘት ያስፈልጋል ማለት ነው። እርግጥ ትርፍራፊ ድምጾች ይኖራሉ እነሱንም የማከፋፈያ ሥርዓት አለ። ዋናው ቁም ነገር ግን በዚህ ሥርዓት መሠረት ፓርቲዎች በህብረተሰቡ ውስጥ እንዳላቸው ክብደት እየታየ በፓርላማው ውስጥ ወንበር ይሰጣቸዋል። 20ሺህ ድምጽ ያገኘ ፓርቲ አንድ ወንበር፣ መቶ ሺህ ድምጽ ያገኘ ፓርቲ 5 ወንበር ወዘተ - - -

ሁለቱም የምርጫ ሥርዓትቶች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጐኖች አሏቸው። የበዙሃን ምርጫ ሥርዓት በፓርላማው ውስጥ ግልጽ የሆነ ብልጫ ስለሚያስገኝ ለተወሰነ ጊዜ ለተመረጠ መንግሥት ቅልጥፍናንና መረጋጋትን ያስገኛል። ግን ደግሞ እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ «ከግማሽ በላይ አንዲት ድምጽ ያመጣ ሁሉም ነገር ሲኖረው ከግማሽ በታች አንዲት ድምፅ የወረዳ ምንም ነገር የለውም። የኢሕአዴግ ንዑስ ሥርዓት ደግሞ ይህ አግጦና አፍጦ የሚታይ ነው።ከየምርጫ ቀበሌው 20ም 30ም ከመቶ እያመጡ ፓርላማ የሚደረሱት ተወካዮች በያለበት 80ም 70ም ከመቶ መራጮችን በየቀበሌው እያራገፉ የመጡ ተወካዮች ይኖራሉ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ለተራ የመንግሥት ምርጫ ምንም ችግር ላይኖረው ይችላል። ይህ መንግሥት እንዲሁ በተራ ምርጫ ከአራትም ከአምስትም ዓመት በኋላ ቦታውን ለሌላ ይለቃለና። እንደ ህገ መንግሥት ላለ ዘላቂና የሁሉንም አግባብ ያገኘ ሰነድ ለማጽደቅ ግን ሌላ ጥያቄ ነው።

ተመጣጣኝ ውክልና ከዚህ አንጻር ሲታይ ማገኛውም የህመንግሥት ኤክስፐርት የማይክደው አወንታዊ ገጽታ አለው። ይበልጥ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ነው። በጠቅላላው በሀገሪቱ አንድም ሁለትም ከመቶ ብቻ ከሚያመጡ ድንክ ፓርቲዎች በስተቀር በህብረተሰቡ ውስጥ አለሁ የሚል ኃይል ሁሉ እንደአቅሙ በፓርላማው ውስጥ ይወከላል። ይህ የምርጫ ሥርዓት እንደ ባለቀለም ፎቶግራፍ ነው የምለው ለዚህ ነው። ይህ መልካም ገጽታው ሲሆን በዚህ መልክ የተቋቋመ መንግሥት ቅልጥፍና ያንሰዋል። ፓርቲላማው «የጨረባ ተዝካር» የሚሆንበት አደጋ አለ። የፈረንሳይ ፓርላማ ከደጉል በፊት፣ የጣልያን ፓርላማ እስከዛሬ ይህ ሁኔታ ይታይባቸዋል። በዚህ የተነሳ ለአራት አምስት ዓመት ለሚመረጥ መንግሥት ይህ የምርጫ ሥርዓት እምብዛም አይፈለግም። ለህገመንግሥት አውጭ ጉባዔ ምርጫ ግን እስከዛሬ ከሱ የተሻለ የምርጫ ሥርዓት አልተገኘም። በቅርቡ በካምቦድያ የተካሄደው ምርጫ አሁን ደግሞ በደቡብ አፍሪካ በመዘጋጀት ላይ ያለው ምርጫ የተቀበሉት ሥርዓት ይኸው ነው።

የኢህአዴግ የምርጫ ሥርዓት ለሀገራችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉን አቀፍ የሆነ ውይይትና ድርድር የሚያስችል አይደለም። ከዚህ አልፎ በየቀበሌው ሲደመሩ ሰባም ሰማንያም ከመቶ የሚሆኑ ዜጎች ያልመከሩበት ወይም የተቃወሙት የአንድ ንዑስ ኃይል ሕገ መንግሥት የሚጸድቅበት ሁኔታ ይፈጠራል። ለምንፈልገው ሰላምና ዱሞክራሲ፣ ሀገራችንና ህዝባችን ለሚያስፈልጋቸው መረጋጋት በጣም አደገኛ ሁኔታ ይፈጥራል። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ህገ መንግሥት ተራ ሕግ አይደለም። ሲጸድቅ ከፍተኛ ስምምነት (ኮንሴንሰ) ያስፈልገዋል የሚባለውን ያህል እንዲሻሻል፣ እንዲለወጥ፣ እንዲ እንተቶ እንድትነካ እንደ ተራ ህግ ተራ ድምጽ ብልጫ አይበቃውም። ሁለት ሶስተኛ፣ ሶስት አራተኛ እየተባለ የተጠናከረ የብዙሃን ድምፅ ያስፈልገዋል።

<u>ጥያቄ</u>፣ ኢህአዴግ ለምን ይህንን ንዑስ ሥርዓት መረጠ?

<u>መልስ</u>፣ ተመጣጣኝ ውክልናን ያልመረጡበት ምክንያት ከሰዎቹ አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። ተመጣጣኝ ውክልና ራሱ ጽንሰ ሃሳቡ ውይይት፣ መግባባት፣ የሌላውን ሃሳብ ክፍት በሆነ አእምሮ ማዳመጥ፣ ከሌላው አስተሳሰብ ጠቃሚ ነገር ሊኖር ይችላል ብሎ ከወዲሁ መዘጋጀት፣. . . እነዚህን ሁሉ የሚጠይቅ ሥርዓት ነው። የኢህአ ዴግ መሪዎች የተማከለ (ቶታሊታሪያን) አስተሳሰብ ለዚህ የተመቸ አይደለም።

እናሱ ጠቅልለው የማይቆጣጠሩት ማንኛውም ተቋም ውስጥ ተሳትፈው ዲሞክራሲያዊ ትግል ለማካሄድ ይህ አሰተሳሰባቸው አይፈቅድላቸውም።

ከብዙሃን የምርጫ ሥርዓት እንኳን 51 ከመቶ በሁለት ዙር የሚለውን ሥርዓት ያልተቀበሉበትና ነገሩን በአንድ ዙር በከፍተኛ ድምጽ ለመጨረስ የሞከሩ በትም ምክንያት ግልጽ ይመስለኛል። ይኸ ደግሞ የፖለቲካ ስሌት ነው።በህብረ ተሰቡ ውስጥ አለን የሚሉት የብዙሃኑ ድጋፍ ጨርሶ እንደሌላቸው ያውቃሉ። በተጭበረበረ የምርጫ ሂደት በመጀመሪያ ዙር ከሚወዳደሩት ተወካዮች 20ም ሰላሳም ከመቶ እያመጡ «ከፍተኛ ድምጽ ተገኝቷል» ብለው የማለፍ ተስፋ አላቸው። በሁለት ዙር ከ50 ከመቶ ቢባል ግን ስእሉ ጨርሶ ይሰያል። ሁለተኛው ዙር ላይ ተቃዋሚዎቻቸው አብረው እንዳይገጥሟቸው ይፈራሉ። ቀላል ምሳሌ ልስጥ። በአንድ አካባቢ ወይም የምርጫ ቀበሌ አንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት እጩ ከድምጹ 35 ከመቶ፣ የኢዴሃቅ እጩ 20 ከመቶ፣ የኢህአዴግ እጩ 40 ከመቶ የቀረውን 5 ከመቶ ደግሞ ሌሎች ትናንሽ ፓርቲዎች ይካፈሉት እንበል። እንደ ኢህአዴግ ሥርዓት ከሄድን 40 ከመቶ ያመጣው የኢህአዴግ እጩ ተመረጠ ይባላል። በሁለት ዙር ከ50 ከመቶ በላይ ከተባለ ግን ሁለተኛው ዙር ላይ ቅንጅቱና ሌሎቹ ተቃዋሚ ኃይሎች ከመሃከላቸው ከፍተኛ ድምጽ ላመጣው ለደኢህዴህ እጩ ቦታቸውን ለቀው የነሱ መራጮች ለሱ እንዲመርጡ ጥሪ ሊያደርጉ ይችላሉ። ኢህአዴግ በተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት ተሸነፈ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ግንባሮች በየቀበሌው ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። በአጭሩ የነሱ ስሌት በየአካባቢው ኢህአዴግ በየምርጫ ቀበሌው እያንዳንዱ ተቃዋሚ ድርጅት ለየብቻው ቆሞ እስከገጠመው ድረስ ከፍተኛውን ድምጽ የማግኘት አነስተኛም ብትሆን እድል አለችኝ ብሉ ያምናል። ሁለትም ሶስትም ድርጅቶች ግን የምርጫ ግንባር ከሠሩበት ነገሩ ጨርሶ ተስፋ እንደሌለው ያውቃል። በህብረተሰቡ ውስጥ የበዙኃኑ ድጋፍ እንደሌለው አናሳ ኃይል እንደሆነ ከኛ በተሻለ ተረድቶታልና።

<u>ጥያቄ</u>፣ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ኰሉኔል ጉሽ«ነገደ ጉበዜ አመራር ላይ መውጣት የለባቸውም» ብለዋል ብለው ያስተጋባሉ። ልዩነታችሁ ምን ላይ ነው?

<u>መልስ</u>፣ የትኛው አመራር ቦታ? እኔ ለአመራር ቦታ ታግዬም አላውቅም። በሀገራችን የእርቅና ሰላም ጉባዔ እንደሚያስፈልግ፣ ይህ ጉባዔ ምን ይዘት እንደሚኖረው ከመኢሶን እንዲሁም ከቅንጅት አመራሮች ጋር ለረዥምም ጊዜ ተወያይተን፣ በዚህ ጉዳይ ሥራዬ ብዬ እንድገፋበት ከቅንጅቱ አመራር ተልእኮ ከተሰጠኝ በኋላ በተቻለኝ የተለያዩ ድርጅቶችን አማክሬ፣ እነሱም በጉዳዩ ቀደም ብለው አስበውበት ስለነበረ በቀላሉ ማስተባበር ስለተቻለ የፓሪሱን ጉባዔ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ፣ ሁሉንም ድርጅቶች በአረካ ሁኔታ አዘጋጀሁ። ይህን ጉባዔ እንኳን ልመራ ቀርቶ አልተሳተፍ ኩበትም። አስተባባሪው ኮሚቴ ሲቋቋም ቅንጅቱ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ እንድወከ ለው መረጠኝ። የኮሚቴው አባላት ደግሞ በሙሉ ድምጽ አስተባባሪ እንድሆን መረጡኝ። ከባድ ሥራና ኃላፊነት ነበር። የተቻለኝን ሠርቻለሁ። ይህ ጉባዔ እንዴት እንደሚታየኝ ከመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ግልጥልጥ አድርጌ ለአባላቱ ተናግሬያለሁ። የትም ቦታ ሳይሆን አዲስ አበባ መደረግ አለበት። ስብሰባው የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ መሆን የለበትም ሲቪል ሶሳይቲውም መወከል አለበት፣ ያገባኛል ብሉ ለመገኘት የጠየቀን ሁሉ በከፍት ልቦና መቀበል መቻል አለብን፣ የጉባዔው ዝግጅት በጣም ግልጽና ዲሞክራሲያዊ መሆን አለበት፣ በጉባዔው ላይ የሀገር ሽማግሌዎች መገኘት አለባቸው፣አጀንዳው ቀደም ብሉ ለህዝብም ለተሳታፊ ድርጅቶ ችም ይፋ መሆን አለበት፣ በዚህ ጉባዔ ዞሮ ዞሮ ኢህአዴግ ስለማይገኝበት አንድ አማራጭ አካል መውጣት ይኖርበታል . . . እነዚህን ሁሉ ለአባላቱ በጽሁፍ አቅርቤ እየተከራከርን እየተፋጨን፣ ገን ደግሞ በወንድማማችነት መንፈስ ተቀራርበን ሠርተናል። በኔ ግምት ጉባዔው የተሳካ ውጤት አስገኝቷል። ኮሚቴው ጋር በአስተባባሪነት ስሰራ ከጉባዔው በኋላ እኔ እንዴት አመራር ላይ እንደምወጣ ሳይሆን ይህ ጉባዔ እንዴት ከፍ ብዬ በጠቀስኩት ዘዴ ይካሄዳል የሚለው ጥያቄ ላይ ብቻ ነበር ያተኮርኩት። በነዚህ ጥያቄዎች ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ነበሩ። ይህንን ወደፊት እንወያይበታለን።

በጉባዔው ዝግጅት ወቅት መድገን ተወካይ ዘንድ ከተገጸባረቁትና ከተከሰቱት አንዳንድ የአሠራር ስልትና የአስተሳሰብ ልዩነቶች በስተቀር እስከዚህም ከባድ ልዩነቶች አልነበሩም። ኰሉኔል ጉሹን አላውቃቸውም። የፖለቲካ ልዩነት አለ ቢባል አንድ ጊዜ አንድ መጽሔት ላይ ያየሁት ቅንጅቱን ትቼ የወጣሁት መኢሶንና ኢህአፓ የግራ ድርጅቶች በመሆናቸው ነው ሲሉ አንብቤያለሁ። የዛሬን አያርገውና እግዜር በሚያውቀው ኢሠፓ ቀኝ አክራሪ ድርጅት አልነበረም። የሆነ ሆኖ እኔ ይኸንን ለትግል ህብረት እንቅፋት የሚሆን ልዩነት አድርጌ አላየውም። የምንፈልጋት ኢትዮጵያ ግራ ሆነ ቀኝ ሁሉም የመሰለውን አስተሳሰብ እየሰበረ፣ በህዝብ ፊት እየተወዳደረ ሲቀናው አሸንፎ፣ ሳይሳካለት ደግሞ እስከሚቀጥ ለው ምርጫ በተቃዋሚነት ተከብሮ የሚኖርባት ኢትዮጵያን ነው። የግራና ቀኙ ጥያቄ ያኔ ይመጣል።

እዚህ ላይ ግን አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ። ይህ ደግሞ ከኰሉኔል ጉሹ አባባል አልፎ የሚሄድ ነው። የዛሬ ሃያ ዓመት ገድም ሁሉም ከኔ ይበልጥ ኰሙኒስት ለአሳር ነው የሚልበት ጊዜ ነበር። ዛሬ ደግሞ ከኔ ይበልጥ ጸረ ተራማጅ እየተባለ ፉክክር የተያዘ ይመስላል። እነዚያ አልባንያ ሲሉ ከርመው እንኳን ለኛ ለአባሉቻቸውም ፍሬቻ ሳያሳዩ ተቀይረናል አሉን። ነገ እንኳን ለሶሻሊስት አብዮት የታገለና እንዲያው የሶሻሊዝም ስም ሲጠራ ፈገግ ያለ ሁሉ ይያዝ ይጠለፍ የሚባልበት ጊዜ ሳይመጣ አይቀርም። በዚህ አያያዝ እኔ በበኩሌ ከእንገዲህ ደሞ በዛ በኩል አሽቅድድም አልችልም። ግራ ነህ ብለው ሊገጥሙኝ የሚፈልጉ ከነዛ ጥላቸው ጋር ይታገሉ እንደሆን እንጂ እኔን አያገኙኝም። ለማንኛውም ግን ሀገሪቱን ግራ ናቸው ከሚባሉ ኃይሉች እናጸዳለን የሚሉ ኃይሉች ካሉ «እጅግም ጡሃራ ከነጃሳ እኩል ነው» የሚለውን የወሉዎች ተረት ላስታውሳቸው። ለዲሞክራሲ አይበጅም።

<u>ጥያቄ</u>፣ እርስዎ ከደርግ ጋር ሥልጣን በተጋሩበት ወቅት ከተቃዋሚ ኃይሉች ጋር እርቅ ሳይፈጥሩ አሁን እንዴት እርቅ ይኑር ይላሉ?

<u>መልስ</u>፣ መጀመሪያ እርቅ በሚለው ሃሳብ መግባባት ያስፈልጋል። እርቅ ማለት ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ መልሶ ይፋቀር፣ ልዩነት የሚባል ነገር ሁሉ ከምድራችን ይጥፋ ማለት አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የዋህነት ነው። እርቅ ሲባል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ወንጀል የፈጸሙ፣ በተካሄዱት ጦርነቶች ሳቢያ በምርኮኞችም ላይ ሆነ በሲቪሉ ህዝብ ላይ አላስፈላጊ የሆኑ አሰቃቂ ግፎች የፈጸሙ ወይም አሁንም በመፈጸም ላይ ያሉ የመንግሥትም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ተጠሪዎች ለፍርድ አይቅረቡ ማለት አይደለም። ፍርድ መቅረብና በሕዝብ ላይ ስለፈጸሙት ግፍ ሕጋዊ በሆነ መድረክ «ሂሣብ ማወራረድ» ይኖርባቸዋል።

እርቅ የምለው ከእንግዲህ በኋላ የፖለቲካ ልዩነቶች ደመኛ ጠላቶች አያድርጉን፣ እነዚህን ልዩነቶች ህዝቡ የሚዳኝበትን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ተጋግዘን እናብጅ፣ ሁላችንም በዚህ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ክልል ውስጥ መታገልን እንማር። በዚህም ተጋግዘን ለሁላችንም ለህዝቡም የሚበጅ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊት አገር ለመገንባት ተባብረን እንስራ ማለት ብቻ ነው።

«እርስዎ ከደርግ ጋር ሥልጣን በተጋሩበት ወቅት. . .» ለተባለው በእውነቱ፡ መኢሶን ከደርግ ጋር የሰራበትን የ20 ወራት እድሜ ዋና መለኩ የሥልጣን መጋራት ጉዳይ አልነበረም። ይህ ዋናው ነጥብ ቢሆን ኖሮ፣ ዓላማችን ሥልጣን መጋራት ቢሆን ኖሮ ተስማምተን፣ አጉብድደን እንደምንም የምንቆይበት ሁኔታ መፍጠር አያቅተንም ነበር። ከመጀመሪያውም አብረን መስራት የጀመርነው ደርግ እርቅቀን የሰጠነውንና በጊዜው ያመንንበትን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በይፋ ስለተቀበለ ነበር። አብረን የሠራንበት ወቀት እስከዚህም የሥልጣን መጋሪያ ወቅት ሳይሆን ሕዝቡን ከዳር እስከዳር ለማደራጀት የተዋደቅንበት ወቅት ነበር። ደርግ ከዚህ ፕሮግራም ከተንሸራተተ፣ የኛም ከሱ ጋር መሥራት ለሀገሪቱ ጉዳት እንጂ ጥቅም የማያመጣበት ሁኔታ ላይ ከተደረሰ ለቀን እንሄዳለን ነበር በግልጽና በይፋ አንል የነበረው። ብዙ ሰው ይህንን አባባላችንን እንደ ተራ ፕሮፓጋንዳ ይወስደው ነበር። ለሀገራችን የጠቀመ እስከመሰለ ድረስ አብረን ሠራን። ጉዳ ሲመስለን ደግሞ የሥልጣን ጥም ሳያታልለን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በገባነው ቃል መሠረት ህቡዕ ገባን።

ለምን አሁን እርቅ ትላላችሁ? ለተባለው ከሁለት አንጻር መመለስ ይቻላል። አንደኛ እኛ ብቻ ሳንሆን ካለፈው መከራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ካነባው የደም እንባ ቅንጣትም ትሁን ትምህርት ቀስሜያለሁ የሚል ዜጋ ዛሬ ችግሮቻችንን ሁሉ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ ውይይት እንፍታ ቢል ምንም እንግዳ ነገር መሆን የለበትም። ሁለተኛ ደግሞ ዛሬ ያለው የሀገሪቱም ሆነ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ከዛሬ 20 ዓመቱ የተለየና ለሰላማዊ ትግልና ለውይይት ያመቸ ሁኔታ ነው ብዬ አምናለሁ።

ካለፈው ትግል የተቀሰመው ትምህርት አለ። ስላመለጡ የታሪክ አጋጣሚዎች፣ የመወያያ ቱታ ስለነሱ መዋከቦች፣ ወደኋላም መለስ ብለን ታሪካችንን ለመመርመርም ሆነ ወደ ፊትም ወደፊት እንደምናመራ ሁኔታዎችን ለመቃኘት ስለገጠለን የፖለቲካ ብስለት . . . ስለነዚህ ሁሉ ወደፊት እገልፃለሁ። ከረዥምም ጊዜ የትግል ልምድ ትምህርት ቀስሜያለሁ እያለ የሚግደረደር ሰው ያለፈውን ሂደትም ሆነ መጭውንም ወቅት ለመቃኘት የሚያስችለው ኩረብታ ላይ እንዳለ መቁጠር አለበት፣ ራሱን። በዚህ መልክ ካለፈው ሂደት የቀሰመውን ትመህርት ለዛሬ ትግሉና ለመጭው ሂደት መቃናት ካላዋለው ከርሞ ጥጃ እንደተባለው ይሆናል፣ በየዕለቱ እንደ አዲስ የሚወለድ ህጻን። እኔ ካለፈው ተምሬያለሁ። ከሁሉ በላይ ደግሞ መጭው ጊዜ ያሰጋኛል።

የደርግንና የኢህአዴግን የመሸናነፍ ሁኔታ ሳየው አንዳንዴ እያደር የእህያ ውድቂያ እየሆነብኝ ተቸግሬያለሁ። እርግጥ በጦሩ ጥያቄ ኢህአዴግ የደርግን ሠራዊት አሸነፈ። ግን የፖለቲካ ሂደቱን ሳየው የደርግን ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ገዥዎች የፈጸሟቸውን ስህተቶች ለመቶኛ ጊዜ፣ ለሺህኛ ጊዜ ኢህአዴግም እየደገማቸው ነው። አሸንፈናል ዝም ብለህ ተገዛ ይሉናል። የአሸናፊዎች ሰላም ይሰብካል። ለተጭበረበረ ምርጫ በመደረግ ላይ ያለው ቀና ደፋ ማለት፣ በልክ ለተሰፋ ህገመንግሥት የሚደረገው መሯሯጥ ይህንን መሠረታዊ ሃቅ አይሸፍነውም። ከዚህም የሚከተለው አስቸጋሪ አዙሪት ግልጽ ይመስለኛል። እንዳለፉት ገዥዎች ይህንን አገዛዝ የሚቃወሙ ትግላቸውን ያፋፍማሉ። ለሰላምና እርቅ ጉባዔው በቀረበው ሰነድ ላይ እንደተቀመጠው ነው።ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ጸረ ዲሞክራሲያዊ ገጽታውን እያጉላ መሄዱ ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ኃይሎችን እነሱም በበኩላቸው ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ያደርጋቸዋል። ትግላቸው እየተፋፋመ ሲሄድ ደግሞ የኢህአዴግ ጸረ ዴሞክራሲያዊ ድርጊቶች እየተበራከቱ እንደሚሄዱ ሳይታለም የተፈታ ነው። በዚህም ይበልጥኑ እየተጋለጠ፣ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እያጣ፣ ለሕልውናውም ከመሣሪያ ሌላ ምንም መመርኮዣ እየጠፋበት ነገ ከዛሬው ይልቅ የዲሞክራሲ ደብዛ የሚጠፋበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም ደግሞ ለሀገሪቱ ሰላም፣ ለሕዝቦቿ እኩልነትና ዲሞክራሲ የቆሙ ኃይሎችን እነሱም መሣሪያ ወደማንሳት እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል። ኢህአዴግ ራሱ በደርግ ሥር ዲሞክራሲ ጠፋ፣ ሰላም ጠፋ ብሎ «ሰላም በትግል» ብሎ በቀየሰው መፈክር ሥር የመሣሪያ ትግል እንዳካሄደው መሆኑ ነው። ባጭሩ ሀገሪቱ ወደሌላ አዙሪት ውስጥ የምትገባበት አደጋ አለ። ለዚህ ነው የሀገሪቱ የዛሬው ሁኔታና በተለይ ደግሞ ከዚህ ሊከተል የሚችለውን የጥፋት ሂደት በመገንዘብ ነገሮች ከቁጥጥራችን ሳይወጡ በፊት ቱታ ወስዶ በርጋታ መወያየት የሚያስፈልገው።

ሁለተኛ ደግሞ ከዛሬ 20 ዓመት ይልቅ ዛሬ ያለው ሁኔታ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል ሁኔታ ነው። የዛሬ 20 ዓመት በዚያ እጅግ ወደኋላ በቀረ ህብረተሰብ ውስጥ መሬት ላራሹን የመሰለ አብዮታዊ ለውጥ በሰላማዊ ውይይት ከሥራ ላይ የማዋል እድል ነበር ብየ አላምንም። የኢትዮጵያ ህዝቦች ከአብዮቱ መፈንዳት በኋላ ያገኟቸውን ድሎች ለማግኘት ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል። ይህ ብቻ አይደለም። በመጀመሪያዎቹ 2 እና ሦስት ዓመታት የተጎናጸፉቸውን ድሎች መልሰው ላለመነጠቅ ሲታገሉ ደግሞ እንደዚሁ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል። እንግዲህ ከሁሉም ወገን የፈሰሰው ደም ፈሶም ቢሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች የጭቆና መሠረት የነበረው ፊውዳል የመሬት ስሪት ፈርሷል። በዚሁ ትግልና ድል ሳቢያ ደግሞ ለሀገሪቱ እድል ወሳኝ የሆነው የብሔሮች ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ ውይይት ሊፈታ የሚችልበት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል። የፖለቲካ ዲሞክራሲንም በሚመለከተው እንደዚሁ ነው። ዛሬ የኢህአዴጉችን ለዚህ መብሰል እጠራጠራለሁ። እንጂ የኢትዮጵያም ህዝቦች ሆኑ የፖለቲካ ኃይሎቻቸው ከረዥም ጊዜ የትግል ልምዳቸው በቀሰሙት ትምህርት ምክንያት ለዲሞክራሲያዊ አሠራር ብቁ ናቸው ብዬ እገምታለሁ።

እንግዲህ ከዛሬ 20 ዓመት ይልቅ ዛሬ ችግሮቻችንን በሰላም እንፍታ ስንል ካለፈው ልምዳችን ተነስተንና ከሱ ትምህርት ቀስመን ችግሮችን በተቻለ በሰላማዊ ውይይት መፍታት ያስፈልጋል ብቻ አይደለም የምንለው። የዛሬውን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመረምር ደግሞ በኢትዮጵያ ታሪክ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ችግሮቻችንን በሰላማዊ ውይይት ለመፍታት የምንችልበት ሁኔታ አለ ብለን ስለምናምንም ነው።

<u>ጥያቄ</u>፣ የአዲስ አበባው የሰላምና እርቅ ጉባዔ ያሳለፈውን ውሣኔ እንዴት ይመለከቱታል?

<u>መልስ</u>፣ በዚህ ጉባዔ እኛ አልተሳተፍንም። ግን የጉባዔውን አካሄድም ሆነ ውጤት በምንተችበት ጊዜ «እሷው ወልዳ አልመሰለም፣ እሷው ጋግራ አልበሰለም» የተባለው ነገር

እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል:: በተለይ የአስተባባሪው ኮሚቴ አባል ድርጅቶች:: ለየት ያለ አስተሳሰብ ሊኖረን ቢችል ከእንግዲህ ወዴት? በሚለው ጥያቄ ላይ እንጂ በጉባዔው አካሄድና ውጤት ላይ ብዙም ሂሳዊ አስተሳሰብ ሊኖረን አይችለም:: ምክንያቱም በጣም ግልጽ ይመስለኛል:: ስንደኛ የተላለፉት ውሳኔዎች አስተባባሪው ኮሚቴ ቀደም ሲል ባሰናዳው ሰነድ የተመረኮዙ ብቻ ሳይሆኑ የፓሪሱንም ጉባዔ ውሳኔዎች ፈለግ የተከተሉ ናቸው:: ሁለተኛ የተሳታፊዎችን ሁኔታ የሚመለከት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሕዝባዊ ማህበራት ማኅበራት፣ የሀገር ሽማግሌዎች እያልን የወሰንነው እኛው በሙሉ ድምጽ ሲሆን ከዚህ ውጭ የሆነ ነገር የለም:: ውጤቱንም በሚመለከት ከዚህ ጉባዔ የሚፈልቁትን ውሳኔዎች ለመከታተልና ለማስፈጸም ብቃት ያለው፣ከተሳታፊዎች የተውጣጣ አካለ እንዲመሠረት በቅድሚያ ተስማምተንበት ሃሳቡን በሰነዱ ላይ አትርበነዋል:: የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ተቋቁሟል:: ይህ ሁሉ የፈለግ ነውና የጠበቅነው ውጤት ስለሆነ በኔ ግምት የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትን ያለአንዳች ማወላወል መደገፍ፣ እንዲጠናከርም በሃሳብም በሌላም በተገኘው ዘዴ ሁሉ መሞከር ያስፈልጋል::

መጭውን ትግል በሚመለከት ይህ ምክር ቤት ከእለት እለት እየተጠናከረ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦችንም ሆነ የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ እየጨመረ የሚሄድ ድጋፍ ለማግኘት በእውነቱ ስለሀገራችን የወደፊት እድል አንድ ዓይነት «ራዕይ» ያለው አካል መሆን ይገባዋል:: ይህ አርቆ አስተዋይነት የዚህ አካል «አማራጭነት» ምን ላይ እንደሆነ ጠንቅቆ መረዳትን ይጠይቃል:: እርግጥ አሁን ያለው መንግሥት ጸረ ዲሞክራቲክ በመሆኑ፣ ለኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ጥቅም የማይበጅ መንግሥት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ከሥልጣን የሚወርድበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለዚህም መታገል ይኖርበታል:: ግን አማራጭነትን ለኢህአዴግ አማራጭነት ብቻ አድርጉ ማየት ትልቅ ስህተት ይመስለኛል:: ከዚህ ባሻገር አማራጭነቱ ከታሪካችን ከወረስናቸው ጉዳ ከሆኑ የአመጽ፣ የጸረ-ዴሞክራሲ፣ በኃይል ላይ ብቻ የተመረኮዘ የሥልጣን ሽግግር ባህል . . . አማራጭነቱ ለነዚህ ሁሉ መሆን አለበት:: አዲስ የሰላም፣ የዲሞክራሲ ባህል የምንገነባበት፣ የህግ የበላይነት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የምናነግስበት፣ አማራጭነት መሆን አለበት:: ሰነዱ ላይ እንዳልነው ሽግግሩን ሕንድ ኃይል ሌላውን ኃይል የሚተካበት ሂደት ብቻ አርጉ ማየት አይቻልም:: ለሀገራችንም፣ ለሕዝቦቻችንም የሚያስፈልጋቸው ከአንድ ጸረ ዴሞክራቲክና ጸረ ሰላም ሥርዓት ወደተሻለ ዴሞክራሲያዊና ሰላም የሚያሸጋግር ሽግግር ነው:: የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በአሠራሩና በዓላማው የዚህ ዓይነቱ ሽግግር ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ መቅረብ ያለበት ይመስለኛል::

ዛሬ የሚያነሳቸው መፈክሮችና የሚተልማቸው የትግል አቅጣጫዎች ከዚህ አርቆ አስተዋይነት ጠባይ ውስጥ የሚካተቱ እንጂ እሱን የሚጻረሩ መሆን የለባቸውም:: ዋና ዓላማው ህብረተሰባችን በሰላም ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚሸጋገርበትን ዘዴ ቀይሶ የዚህ እውን መሆን መታገል ነው::በዚህ ዓላማ ክልል ውስጥ በመጭው ጊዜ የሚያተኩርበትን የትግል አቅጣጫ በሚገባ መቀየስ ካልቻለ ከፓሪሱ ጉባዔ ወዲህ ለሰላምና ለዲሞክራሲ ትግላችን የታየው የአማራጭ ኃይሎች አንድነት እንዳይበረዝ፣ ለዚህ ትግል በአዲስ መንፈስም የተነሳሳው የሕዝቡ የትግል ወኔ ቅስሙ እንዳይሰበር እፈራለሁ:: ለዚህ በኔ ግምት ምክር ቤቱ ተሉ ተሉ ሁሉንም የሚያሰባስብ፣ በኢትዮጵያ ህዝቦችም ዘንድ ሆነ በዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ እየጨመረ የሚሄድ ድጋፍ የሚያስገኝ የትግል ዓርማ ይዞ መራመድ ይጠበቅበታል::

በኔ ግምት በሚመጡት ወራት ሁሉም መንቀሳቀስ ያለበት በሰነዱ ላይ እንደ ተቀመጠው ነጻና ርትአዊ ምርጫ በሚለው ጥያቄ ላይ መሆን አለበት እላለሁ:: እዛው ሰነዱ ላይ እንደ ተቀመጠው ለኛም ለኢህአዴግም ይህ ወሳኝ ጥያቄ ነው፣ ቀላል ጥያቄ ይመስላል እንጂ:: ለኢህአዴግ ይህ ጥያቄ ልክ እንደሰላምና እርቁ ጉባዔ የማይዋጥ የማይተፋ ጥያቄ ነው:: ዛሬ በውስጥም በውጭም ስለነጻ ምርጫ ምንነት የጋራ የሆኑ፣ እኛ ሙሉ በሙሉ የምንቀበላቸው ኢህአዴግ ግን በምንም ዓይነት በህዝብ ትግልና በውጭ ወዳጆች ተጽእና ካልሆነና ሥልጣን ለቆ በተቃዋሚነት ትግሉን በዴሞክራሲያዊ ዘዴ ለመቀጠል ካልወሰነ በስተቀር የማይቀበላቸው የነጻ ምርጫ መስፈርቶች አሉ:: ግን ደግሞ አማራጭ ኃይሎች ግልጽ የሆነ አቋም ይዘው በዚህ ላይ ብቻ አተኩረው ከታገሉት ይህንን ድፍን ኢትዮጵያና ድፍን ዓለም የሚቀበለውን ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ አቋም በቀጥታ መቃወም በጣም ይቸግረዋል:: ስለሆነም ክርክሩ፣ ልዩነቱ፣ ጠቡ በዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ላይ ሳይሆን በሌሎች አጫፋሪ ጥያቄዎች ላይ እንዳሆንለት ወይም እንዲመስልለት ይፈልጋል:: እንዲህ ዓይነቱ ወጥመድ ውስጥ ገብተው እንዳይዳከሩ ነው:: ለጉባዔው በቀረበው ሰነድ ላይ አማራጭ ኃይሎች በነጻና ርትአዊ ምርጫ ላይ ማተኩር አለባቸው::

ሌላ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ውሳኔ ተላልፏል:: «እንደተፈራው» የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ በጉባዔው ማግሥት ሌላውን ሁሉ ቆምነገር ትቶ ያተኮረው እዚህ ጥያቄ ላይ እንደነበረ አይተናል:: የሰው ልጅ መብት ይከበር፣ ነጻና ርትአዊ ምርጫ ይካሄድ፣ መጭው ህገመንግሥት የሚረቅበትና የሚጸድቅበት ሂደት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያካትት ብለው ወሰኑ አላለም:: ሌላ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ተብሎ ለምን ተጠየቀ ማለቱ አይደለም:: በኢትዮጵያ ነጻ ምርጫ እንዲደረግ ዋና ዓላማዎችን እስከሆነ ድረስ አስፈላጊ ከሆነ ለዚህ ምርጫ ሁኔታውን ለማመቻቸት ሌላ መንግሥት እንዲቋቋም መጠየቅ ተገቢ ሊሆን ይችላል:: ኢህአዴግ ዘላቂና የማያወላዳው ዴሞክራሲያዊ ጥያቄያችንን በዚህ በመንግሥት ጥያቄ አከላልሶና አድበስብሶ ለማለፍ መንገድ የማይሰጥ ሁኔታ እስከሆነ ድረስ::

በተጨባጭ የኖ የአማራጭ ኃይሎች መጭው ተግባር እንግዲህ ግልጽ ይመስለኛል:: ከሁሉ አስቀድሞ የትኩረት ትኩረት መስጠት ያለብን ባስቸኳይ ነጻ ምርጫ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ፣ ከዚህ አንጻር የኢህአዴግን የምርጫ ሂደት በምን በምን እንደምንቃወም፣ ነጻና ርትአዊ ምርጫ እንዲደረግ ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው የሚዘረዝር አንድ መግለጫ (ሚሞራንደም) መውጣት ይኖርበታል:: ለዚህም ከሁሉም የተውጣጣ አንድ ኮሚሽኑ ማቋቋም አጣዳፊ ተግባር ይመስለኛል::

ሁለተኛ ይህንን ሰነድ ህዝቡም ሆነ ዓለም አቀፉ ኮሙኒቲ በደንብ እንዲረዳው ማድረግና ድጋፉን እንዲሰጠው ከፍተኛ የቅስቀሳ ዘመቻ መካሄድ አለበት:: ከኢህአዴግ ጋር የሚደረጉ ድርድሮች በዚህ ይፋ በሆነና የህዝብ ድጋፍ ባለው አቋም ላይ ተመርኩዞ ይሆናል::አማራጭ ኃይሎች ከኢህአዴግ ጋር ሲደራደሩ ለዚህ ዓላማ፣ ይህንን አቋም ይዘው መሆኑ ከወዲሁ ግልጽ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው:: በሚመጡት ወራት ባለፈው አንድ ዓመት እንዳዳረግነው በጋራ ህዝቡንም ሆነ ዓለም አቀፉን ኮሙኒቲ ከጉናችን አሰልፈን ወደፊት መጓዝ የምንችለው በዚህ መልክ ይመስለኛል::